የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ-መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 21
ADDIS ABABA- 8th March, 2006

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፰/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት አዋጅ......
ገጽ ፫ሺ፫፻፺፭

CONTENTS

Proclamation No. 488/2006

Ethiopian Organic Agriculture System Proclamation ....
Page 3395

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፰/፲፱፻፺፰

## የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት ለመዘርጋት የወጣ አዋጅ

በተፈጥሮ ለሚመረቱ የግብርና ምርቶችና ከእነዚሁ ለሚገኙ የምግብ ሸቀጦች በሸማቾች በኩል ያለው ፍላጐት በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ በመምጣቱ በሀገራችን በተፈጥሮ ግብርና ሊመረቱ ለሚችሉ ምርቶች አዲስ ገበያ የሚፈጥር በመሆኑ፤

እንደእነዚህ ላሉት ምርቶች ያለው የገበያ ዋጋም ከፍተኛና ለገጠሩ ኅብረተሰብ የተሻለ ዋጋና የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስገኘት ጠቀሜታ ያለውና የአመራረት ዘዴውም የመሬትን ለምነት፣ ብዝሃ ሕይወትንና የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ፤

እያደገ የመጣውን የምርቱን ተፈላጊነት ለማርካትም የግብርና ምርቶችና የምግብ ሸቀጦች በተፈጥሮ ወይንም ሰው ሰራሽ የሆነ ኬሚካል ጥቅም ላይ ሳይውል የተመረቱ መሆናቸውን የሚገልጹ ወይንም ይህ ዓይነቱ እንድምታ ያላቸው ምልክቶች እየተደረጉባቸው ለሸማቾች በገበያ ውስጥ በመቅረብ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ማሳየቱ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በሀገራችን በመካሄድ ላይ የሚገኘው የግብርና ምርቶች የአመራረት ሥርዓት የተፈጥሮ ግብርና አመራረት ዘዴ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟላና በቀላሉ ምርቱን ለዓለም ገበያ ማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 488/2006.

## A PROCLAMATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN ORGANIC AGRICULTURE SYSTEM

**WHEREAS,** consumers' demand for organically produced agricultural products and foodstuffs is globally increasing and thereby a new market for the country's organically produced agricultural products is being created;

**WHEREAS,** the market price for such products is higher, and contributes towards the attainment of better price and economic perspective for the rural population while the way in which they are produced involves less intensive use of land and the protection of biodiversity and the environment;

**WHEREAS,** in response to the rising demand, for such agricultural products and foodstuffs are being placed on the market with labels stating or implying to customers that they have been produced organically or without the use of synthetic chemicals. Therefore, it is necessary to show to the customers that proper labeling of organic agricultural products is essential;

**WHEREAS,** the way in which all agricultural products produced in the country fulfills the requirements of organic agricultural production methods and gives the possibility of easily supplying the products in the international market;

ለተፈጥሮ የግብርና ምርቶች ገበያ ያላቸው አገሮችም እንደእነዚህ ያሉትን ምርቶች ለመጠቀም የሚያስችሉ ደንቦችን ያፀደቁና የኢንስፔክሽን ሥርዓቶችንም የዘረጉ በመሆናቸው፤

የተፈጥሮ የአመራረት ዘዴዎችን በመጠቀም የተመረቱ መሆናቸውን የሚገልጹ ምልክቶች የሚደረጉባቸው የግብርና ምርቶችን በሚመለከት የአምራቾችንና የሸማቾችን ጥቅም ለማስጠበቅ መሟላት የሚገባቸውን መሠረታዊ መስፈርቶች በሀገራችንም በግልጽ ማስቀመጥ የሚገባ በመሆኑ፤

ይህም የአመራረት፣ የአደረጃጀትና የአሰረጫጨት ሥርዓት በሌሎች አገሮች የተለመደና ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በአገራችን እንዲሰራበት በተፈጥሮ ዘዴ የተመረቱ መሆናቸውን የሚጠቅሱ ምልክቶችን የሚጠቀሙ ኦፕሬተሮች የተወሰኑትን መሠረታዊ መስፈርቶች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ ዕውቅና ባላቸው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት በመደበኛነት በሚከናወኑ የክትትል ሥርዓቶች ውስጥ ማለፍ የሚገባቸው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## ክፍል አንድ
## ጠ ቅ ላ ላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፰/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው፤

፪/ "እውቅና" ማለት የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ኢንስፔክሽን ለማድረግና የሰርተፊኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ብቃት ያላቸው ስለመሆኑ ሚኒስቴሩ በይፋ እውቅና የሚሰጥበት ሥርዓት ነው፤

፫/ "የግብርና ምርት" ማለት በጥሬው ወይንም በተዘጋጀ መልኩ ከግብርና ተግባራት የመነጨና ለሰው ፍጆታ ወይንም ለእንስሳት መኖ ለገበያ የሚቀርብ ማናቸውም አይነት ምርት ወይንም ሸቀጥ ነው፤

**WHEREAS**, countries that represent important target markets have already adopted rules and inspection arrangements for the use of such products;

**WHEREAS**, in the interests of producers and consumers of products bearing labels referring to organic production methods, the country should prescribe the minimum requirements which must be complied therewith;

**WHEREAS**, it is necessary to adopt this internationally accepted production, processing and distribution system in our country; and all operators using labels referring to organic production should be subjected to regular follow-ups, carried out by accredited inspection and certification bodies, to ensure that they meet the prescribed minimum requirements;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Organic Agriculture System Proclamation No. 488/2006."

### 2. Definitions

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ "Ministry "means the Ministry of Agriculture and Rural Development;

2/ "accreditation" means the procedure by which the Ministry formally recognizes the competence of inspection and certification bodies to provide inspection and certification services;

3/ "agricultural product" means any product or commodity, raw or processed, originating from agricultural activities and marketed for human consumption or animal feed;

፬/ "የተፈጥሮ ግብርና ምርት" ማለት በአመራረቱ፣ አደረጃጀቱና በአሰረጫጨቱ ሰው ሰራሽ የሆኑ የኬሚካል ግብአቶችን ያልተጠቀመና በጀኔቲክስ ምህንድስና ዘዴ ያልተመረተ ወይንም ያልተዘጋጀ ምርት ነው፣

፭/ "እንስሳት" ማለት ለምግብነት ወይንም ለምግብ ዝግጅት የሚውሉ የቀንድ ከብቶችን፣ አሣማዎችን፣ ፍየሎችን፣ በጎችን፣ የጋማ ከብቶችን፣ ዶሮዎችንና ንቦችን የመሳሰሉ የቤት ወይም በለማዳነት የሚረቡ እንስሳትን ያካትታል፤

፮/ "የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ሥርዓቶች" ማለት በሚኒስቴሩ በግልጽ የጸደቁ ወይንም እውቅና የተሰጣቸው ሥርዓቶች ናቸው፤

፯/ "ኢንስፔክሽን" ማለት ምርቶች በተፈጥሮ ግብርና ምርት መስፈርት መሠረት መመረታቸውን፣ መዘጋጀታቸውንና መሰራጨታቸውን ማረጋገጥ ነው፣

፰/ "ኦዲት" ማለት የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት ሂደቶችና ተያያዥነት ያላቸው ውጤቶች ከሚጠበቁባቸው ግቦች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለመወሰን ስልታዊና ገለልተኛ በሆነ አሠራር የሚከናወን የማረጋገጫ ዘዴ ነው፤

፱/ "ሰርተፊኬሽን" ማለት እውቅና የተሰጣቸው የሰርተፊኬሽን አካላት የግብርና ምርቶች የቁጥጥር ዘዴዎች የሚፈለጉ መሥፈርቶችን የሚያሟሉ ስለመሆናቸው በጽሑፍ ወይንም ተመጣጣኝነት ባለው ሌላ መንገድ ማረጋገጫ የሚሰጡበት ሥርዓት ነው፤

፲/ "የሰርተፊኬሽን አካል" ማለት "በተፈጥሮ የተመረተ" በሚል ስያሜ የሚሸጥ ወይንም ይኸው ምልክት የተደረገበት የግብርና ምርት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትሎ የተመረተ፣ የተዘጋጀ፣ እንዲያዝ የተደረገ፣ ለውጭ ገበያ የቀረበ ወይም ከውጭ ወደ አገር የገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ኃላፊነት የተሰጠው የራሱ መለያ ምልክት ያለው ነጻ አካል ነው፤

፲፩/ "ምልክት" ማለት የኢንስፔክሽንና የሰርተፊ ኬሽን አካላት የሚታወቁበት በኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ተመዝግቦ ዕውቅና ያለው የሕግ ጥበቃ የሚደረ ግለት የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች መለያ ሆኖ የተፈጥሮ ግብርና ምርትን ለማስተ ዋወቅ በምርቱ ማሸጊያ ላይ የተጻፈ፣ የታተመ መሆኑን በግራፊክ መልክ የተቀረፀ ወይንም ከምርቱ ጋር አብሮ የሚቀርብ ወይንም ከምርቱ አጠገብ የሚታይ ምልክትነው፣

4/ "organic agricultural product" means a product which is produced, processed or handled and distributed without the use of synthetic chemicals and genetically modified organism;

5/ "livestock" means any domestic or domesticated animal such as bovine, porcine, caprine, equine, sheep, poultry and bees raised for food or for use in the production of food;

6/ "Inspection and certification systems" means systems, which have been formally approved or recognized by the Ministry;

7/ "Inspection" means the examination of production, processing and distribution of organic agricultural products based on organic agricultural production standards;

8/ "audit" means a systematic and functionally independent examination of organic agriculture system to determine whether activities and related results comply with defined objectives;

9/ "certification" means the procedure by which recognized certification bodies provide written or equivalent assurance that agricultural products' control systems conform to requirements; -

10/ "certification body" means an independent firm having its own logo, which is responsible for verifying that an agricultural product sold or labeled as "organic" is produced, processed, handled, exported or imported according to this Proclamation and regulations as well as directives issued hereunder;

11/ "logo" means a symbol, printed or graphic matter meant for the identification of certification and inspection body which has legal protection and registered under the Ethiopian Intellectual property right protection office; affixed to the package of organic product, or accompanies or is displayed near the product for the purpose of promoting it;

፲፪/ "ኦፐሬተር" ማለት የተፈጥሮ የግብርና ምርቶችን ለገበያ ለማቅረብ የሚያመርት፣ የሚያዘጋጅ፣ ምልክቶችን የሚያደርግ፣ ወደ ውጭ የሚልክ ወይንም ከውጭ አገር የሚያስገባ በኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካሉ ሰርተፊኬት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፣

፲፫/ "የተፈጥሮ ግብርና ምርት ካውንስል" ማለት የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የሚያቋቁመው ሆኖ ከኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካላትና ኦፐሬተሮች አባል የሆኑበት በሰርቲፊኬሽንና በኢንስፔክሽን ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን የሚያይ አካል ነው

፲፬/ "የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች መስፈርት መመሪያ" ማለት ሚኒስቴሩ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች እንዴት እንደሚመረቱ፣ እንደሚደራጁና እንደሚሰራጩ የሚያዘጋጀው መስፈርት ነው፣

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ የተፈጥሮ ግብርና አመራረት ሥርዓትን በመከተል የተመረቱ መሆናቸውን የሚገልጹ ምልክቶች በሚይዙ ወይንም እንዲይዙ የሚደረጉ የግብርና ምርቶች አመራረት፣ አዘገጃጀት፣ አስተሻሸግ፣ ምልክት አደራረግ፣ ክምችት፣ ማጓጓዝ፣ ግብይት፣ ለውጭ ገበያ መላክና ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን በተመለከተ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ፬. ዓላማ

የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩/ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ዕውቅና እንዲያገኝ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፤

፪/ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ተፈላጊነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ገበያዎች ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

፫/ አሳሳች የሆኑ ምልክቶችን በመጠቀም በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ሸማቾች ላይ የማጭበርበር ተግባሮች እንዳይፈጸሙባቸው የመከላከል፤

፬/ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች በሚመረቱበት፣ በሚከማቹበት፣ በሚጓጓዙበትና ለገበያ በሚቀርቡበት ወቅት ኢንስፔክሽን የተደረገባቸውና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ መሥፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤ እና

12/ "Operator" means any person who has a certificate issued from the inspection and certification bodies to produce, process, label, export or import with a view to the subsequent marketing of organic agricultural products;

13/ "Organic agricultural product council" is a council which shall be established by the Ministry of Agriculture and Rural development; and the members comprising from inspection and certification bodies and operators: whose function is to resolve issues on certification and inspection operationS.

14/ "Organic Agriculture production standard directives" is a standard directive, which shall be prepared by the Ministry on how organic agricultural products are produced, processed and distributed.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to the production, processing, packaging, labeling, storing, transportation, marketing, exportation and importation of agricultural products which carry or are intended to carry labels referring to organic production methods.

## 4. Objectives

The objectives of this Proclamation are to:

1/ Facilitate international recognition and acceptance of the Ethiopian organic agriculture system;

2/ Ensure the introduction of Ethiopian organic agriculture products in the relevant international markets;

3/ protect consumers of Ethiopian organic agricultural products against fraudulent acts to be committed by the use of misleading labels;

4/ Ensure that all stages of production, processing, storage, transport and marketing of organic agricultural products are subject to inspection and comply with the standards specified by regulations and directives issued hereunder; and

፭/ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች አመራረት፣ ሰር ተፊኬሽንና ምልክት አደራረግ ድንጋጌዎች ለሁሉም ኦፐሬተሮች ወጥነት ያላቸው እንዲ ሆኑ የማድረግ::

## ክፍል ሁለት
## የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ሥርዓት

### ፭. ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት

ማንኛውም የተፈጥሮ ግብርና ኦፐሬተር እውቅና በተሰጠው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካል በመመዝገብ ራሱን ለሀገሪቱ የተፈጥሮ ግብርና ምርት ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ሥርዓት ተገዥ የማድረግ ግዴታ አለበት::

### ፮. የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት

ማንኛውም እውቅና የተሰጠው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

፩/ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱት እንዲ ሁም አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ መመዘ ኛዎች መሟላታቸውን የማረጋገጥ፤

፪/ ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ ጽሕፈት ቤቱ ንና መገልገያዎቹን እንዲሁም በሥሩ የተመ ዘገቡ ኦፐሬተሮችን እንዲመረምር የመፍቀድ፤

፫/ ሚኒስቴሩ ተግባሩን ለመወጣት አስፈላጊ ና ቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች የመስጠት፤

፬/ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አገልግሎት የሰጣቸውን ኦፐሬተሮች በሚመለከት አመታዊ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ የማቅረብ::

## ክፍል ሦስት
## የእውቅናና የክትትል ሥርዓት

### ፯. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ዕውቅና በሚሰጣቸው የኢንስፔክሽንና የሰርተ ፊኬሽን አካላት ሥራ ላይ የሚውል የተፈጥሮ ግብርና መስፈርት መመሪያ የማውጣት፣

5/ Harmonize provisions for the production, certification, and labeling of organic agricultural products for all operators.

## PART TWO
## INSPECTION AND CERTIFICATION SYSTEM

### 5. Entities Subject to Control

Every operator of organic agricultural products shall be obliged to register with an accredited inspection and certification body and to comply with the national organic agricultural product inspection and certification system.

### 6. Inspection and Certification Bodies

Any accredited inspection and certification body shall be obliged to:

1/ Ensure the fulfillment of requirements provided for by this Proclamation and regulations and directives issued hereunder as well as the relevant international standards;

2/ Alow the Ministry access to its offices and facilities as well as to operators registered with it for audit purposes as may be necessary;

3/ Provide any information required by the Ministry in the course of discharging its duties;

4/ Submit to the Ministry its annual reports on inspection and certification service render to operators.

## PART THREE
## ACCREDITATION AND SUPERVISIO SYSTEM

### 7. Powers and Duties of the Ministry

The Ministry shall have the powers and duties to:

1/ issue directives on organic agricultural production standards to be implemented by the accredited inspection and certification bodies;

፪/ ለኢንስፔክሽንና ሠርተፊኬሽን አካላት ዕውቅና የመስጠት፤

፫/ እውቅና በሚሰጣቸው የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ሥራ ላይ የሚውል የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን ሥርዓት የመመስረት፣ ተግባራዊ እንዲሆን የመከታተልና ቁጥጥር የማድረግ፤

፬/ የተፈጥሮ ግብርናን የሚመለከቱ ተግባራትና ሕግጋት አግባብነት ካላቸው ዓለም አቀፍ ሕግጋት ጋር የተቀናጁና የተጣጣሙ እንዲሆኑ እያጠና የማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ የማድረግ፤

፭/ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት ከዓለም አቀፍ አሠራር ጋር የተገናዘበና ተመሳሳይነት ያለው በማድረግ ሀገራዊና ዓለም አቀፍዊ ከሆኑ ተቋማትና ማህበራት ጋር ቅንጅት የሚፈጥርበትን ዘዴ የመሻት፤

፮/ የአገሪቱ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች በዓለም አቀፍ ዋና ዋና ገበያዎች ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመወሰድ፤

፯/ በኢንስፔክሽንና በሰርተፊኬሽን አካል የተሰጠው ሰርተፊኬት በዓለም ደረጃ እንዲታወቅ የፕሮሞሽን ሥራ መሥራት፣ እስኪታወቅ ድረስም ተመሳሳይ ሥራ ከሚያካሂዱ ሌሎች ዓለም አቀፍ አካላት ጋር እንዲሰሩ ማድረግ፣

፰/ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በሚገባ ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለሌሎች መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች በውክልና የመስጠት፡፡

፱/ የተፈጥሮ ግብርና ምርት ካውንስል ማቋቋም፣ ተግባሩንና ኃላፊነቱን መወሰን፣

፲/ ዕውቅና ሲሰጥ መፈጸም ያለባቸውን የአገልግሎት ክፍያዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስወሰንና እንዲሰባሰብ የማድረግ፣

፲፩/ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ላይ ሊወሰዱ ስለሚችሉ እርምጃዎች መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈጸም፤

፲፪/ ለተፈጥሮ ግብርና ሥርዓት መዳበር የሚያግዙ የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የሥልጠና ፕሮግራሞች እንዲጠናከሩ የማድረግ፤

2/ give accreditations to inspection and certification bodies;

3/ Establish an inspection and certification system, that shall be implemented by accredited inspection and certification bodies and monitor and follow up the implementation;

4/ conduct a study on the conformity and harmony of the countries organic agriculture laws and its implementation with relevant international rules; and implement same upon approval;

5/ establish ways of coordination with national and international institutions and associations with a view to harmonizing the organic agriculture system of the country with international practices;

6/ take all necessary measures so that the countries organic agricultural products gets acceptance in major international market;

7/ advertise the certificate issued by the inspection and certification bodies to be recognized internationally and establish work relationship with international institution carrying out similar activitles in the exercise of their function;

8/ delegate its powers and duties to other government organs to the extent necessary for the proper implementation of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder;

9/ establish an organic agricultural production council and define its duties and responsibilities;

10/ Propose and cause the collection of accreditation service charges rendered by it; upon approval by the council of ministers;

11/ /prepare guidelines and directives pertaining to measures to be taken regarding/ against inspection and certification bodies which do not properly execute their functions;

12/ cause the enhancement of extension services and training programs which can promote the country's organic agriculture system; and

፲፫/ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ግብርና ምርት ሥርዓትና የዚህ አዋጅ አፈጻጸም በየጊዜው እንዲገመገም የማድረግ፤

## ፰. የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ሥርዓት ካውንስል

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፱ መሠረት የሚቋቋመው የተፈጥሮ ግብርና ምርትና ሥርዓት ካውንስል ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

፩ በሚኒስቴሩ የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢና አንድ ፀሐፊ፣

፪/ ከኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አንድ አባል፣

፫/ ከብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት አንድ አባል፣

፬ ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አንድ አባል፣

፭/ ከግሉ የግብርና ልማት ዘርፍ የሚወከል አግባብነት ያለው አንድ አባል፣

፮/ ከንግዱ ሕብረተሰብ የሚወከል አግባብነት ያለው አንድ አባል፣ እና

፯/ ከኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካላት የሚወከል አንድ አባል፣

## ፱. የካውንስሉ ተግባርና ኃላፊነት፣

ካውንስሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

፩/ የዕውቅና ጥያቄ የሚያቀርቡ የሰርተፊኬሽንና የኢንስፔክሽን አካላት ቴክኒካዊ የሆኑ ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ እንዲሁም ዕውቅና በተሰጣቸው ላይ የክትትል ምርመራ በማከናወን ለሚኒስቴሩ ለአስተያየት ማቅረብ፣

፪/ የቀጥታ ምርመራ ስለሚደረግበትና የምርመራ ናሙናዎች ስለሚወሰዱበት ሁኔታ የማጥናትና የመወሰን፣

፫/ የተፈጥሮ ግብርና ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አካላትን ሪፖርቶች የመገምገም፣

፬/ ሥራቸውን በአግባቡ ለማይወጡ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ወይም ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ ዕውቅናቸው ለተወሰነ ጊዜ እንዲታገድ የማድረግ፣

13/ conduct regularly assessment and evaluation of the Ethiopian organic proclamation system and its implementation.

## 8. Organic Agricultural production system council

The council to be established in accordance with Article 7 Sub Article 9 of this proclamation shall be accountable to the ministry and shall have the following members.

1/ a chairman and secretary designated by the Ministry

2/ a member from Ethiopian Institute of Agricultural research

3/ a member from Ethiopian institute of biodiversity

4/ a member from Ethiopian Environmental Protection Authority

5/ a member in the appropriate field representing the private agricultural development sector

6/ a representative from the business community

7/ a representative from inspection and certification bodies

## 9. Powers and Duties of the council

The council shall have the following powers and duties to:

1/ carry out technical initial audits on certification and inspection bodies applying for accreditation, and supervision audits on the accredited ones and submit to the ministry for comments

2/ study and define the conditions of direct auditing and sampling checks;

3/ evaluate the audit reports of organic certification and inspection bodies;

4/ give written warnings to or, upon notifying the Ministry, temporarily suspend the accreditation of inspection and certification bodies which do not properly execute their functions;

፭/ ሥራቸውን በአግባቡ በማይወጡ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አካላት ላይ መውሰድ ስለሚገባው ዕውቅናን የመሰረዝ እርምጃ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፣

፮/ ለተፈጥሮ ግብርና ኦፐሬተሮች የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና የአፈጻጸም መከታተያዎችን የማዘጋጀት

፯/ ስላከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራትና ስለተገኙ ውጤቶች በየዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማቅረብ፣

## ፲. የካውንስሉ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

ሰብሳቢው ሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት፣

፩/ የካውንስሉን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣

፪/ የካውንስሉን ስብሰባዎች ይጠራል፣ በሊቀመንበርነት ይመራል፣

፫/ የካውንስሉን ውሳኔዎች ለሚኒስቴሩ እያቀረበ በማፀደቅ በሥራ ላይ ያውላል፣

## ፲፩. የካውንስል ስብሰባ፣

፩/ ካውንስሉ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

፪/ ካውንስሉ የራሱን የስብሰባና የአሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣

## ፲፪. ክፍያዎች

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚደረገው ክፍያ ሚኒስትሩ መንግሥትን በማስፈቀድ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

## ፲፫. ዝርዝር የተፈጥሮ ግብርና ድንጋጌዎች

፩/ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች በእርሻ ላይ የሚኖራቸውን የአመራረት ዘዴ፣ የተባይ መከላከልን፣ የተፈቀዱ ሥነሕይወታዊ መከላከያ ዘዴዎችን፣ ማጓጓዝን፣ ማከማቸትን፣ ማዘጋጀትን፣ ምልክት አደራረግንና ማስተዋወቅን እንዲሁም መሠረታዊ የኢንስፔክሽን መመዘኛዎችን፣ የጥንቃቄ እርምጃዎችንና ለኢንስፔክሽንና ለሠርተፊኬሽን አካላት ዕውቅና አሠጣጥን በሚመለከት መሟላት የሚገባቸው መሥፈርቶች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦች ይወሰናሉ::

5/ propose to the Ministry the cancellation of the accreditation of certification and inspection bodies which do not operate properly;

6/ Prepare manuals and check-lists for operators of organic agriculture;

7/ Submit to the Ministry annual reports on its major activities and achievement

## 10. Powers and duties of the chairman of the council

The chairman of the council shall subject to the general directives of the ministry;

1. Co-ordinate and administer the activities of the council;
2. Call and preside over meetings of the council;
3. Execute decisions given by the council upon approval by the ministry;

## 11. Meeting of the council

1/ the council shall call or held meeting through the chairman when it is found necessary.

2/ the council shall draw work directives and meetings.

## 12. Fees

The fees to be paid for service rendered by the ministry pursuant to this proclamation shall be fixed by directives issued by the ministry subject to approval by the government;

## 13. Detailed Organic Agriculture Rules

1/ The procedures of organic production at farm level, pest management, permitted biological control, transportation, storage, processing, labelling, advertising and minimum inspection requirements as well as inspection and precautionary measures and accreditation requirements for inspection and certification bodies shall be prescribed by regulations to be issued hereunder.

፪/ በተፈጥሮ ግብርና የእጽዋት አመራረትንና የእንስሳት እርባታን በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦች ያልተደነገገ ከሆነ ሚኒስቴሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ መመዘኛዎች ተቀባይነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

፲፬. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የግብርና ምርቶች ዓርማ

ሚኒስቴሩ፣

፩/ የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ግብርና ምርቶች ዓርማ ይወስናል፤ እንዳስፈላጊነቱም እንዲለወጥ ያደርጋል፤

፪/ ዓርማውን ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎችንና ክፍያዎችን ይወስናል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፭. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፮. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፲፯. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት 30 ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ Where detailed organic production rules for livestock and plant products are not provided for by regulations issued hereunder, the Ministry may cause other relevant internationally accepted standards to be recognized and applied.

14. The National Brand for Organic Products

The Ministry shall:

1/ determine the brand of Ethiopian organic products, and alter same when necessary; and

2/ Define the conditions and payments for the use of the brand.

## PART FOUR
## MISCELLANEUS PROVISIONS

15. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives for the implementation of this Proclamation and regulations issued hereunder.

16. Inapplicable Laws

No law, regulation, directive or practice shall, in so far it is inconsistent with this Proclamation, have effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

17. Effective Date

This Proclamation shall come into force as the date of their publication in the Federal Negarit Gazetz.

Done at Addis Ababa, this 8th day of March 2006

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA